# ኢትዮጵያንስ ሐረር አያርጋት !

በያገርሰው ጥበቡ  yagersew67@gmail.com

03-10-16

"ኢትዮጵያ ሐረር ትሆናለች" የሚለው ንግግር ሁሌም የሚታወስ የታላቁ መሪ የቀድሞ ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ መለስ ዜናዊ ንግግር ነው፡፡ እኔ ደግሞ ኢትዮጵያስ ሐረርን መሆን ይቅርባት፡ ኢትዮጵያስ ሐረር አትሁን እላለሁ፡፡ ያለፈው ዘመን ቅኝቷ ፤ ስለሐረር ይሰማ፡ይዘመር፡ይዘፈን የነበረው የመቻቻል እና የፍቅር ከተማ መለያ፡ የእርሳቸውን ንግግር ለማለት እንደሚያበቃ ግን አምናለሁ፡፡ ይህ ፅሁፍ እርሳቸውን ለመሞገት ሳይሆን የዛሬ ስምንት አመት ሲናገሩ ኢትዮጵያን የተመኙላት  ሐረርን መሆን ዛሬ የለችምና ነው፡፡ አሁንማ መቻል እንጂ መቻቻል እንደቀረ፤ አፈናና አምባገነንነት ያጀበው ጠባብ ብሔርተኝነት እና የተንኮል መረብ እንደወረራት የሚሰማ ጀሮ፤ የሚያስተውል ልቦና ጠፍቷልና አገሬ እንደሐረርስ አትሁን እላለሁ፡፡ በመላው ኢትዮጵያ አያሌ የልማት እና መልካም አስተዳደር ጉዳዮች ትኩረት ተሰጥቷቸው ከፍተኛ ርብርብ ሲደረግ፤ በተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች ግዙፍ ፕሮጀክቶች ሲጀመሩ ፤ሲጠናቀቁ ፤ሲጀመሩ.... ለውጥ በመላው ኢትዮጵያ በየደጃፉ እየታየ ነው፡፡ አሁን ደግሞ የመልካም አስተዳደር መሻሻል ለማስመዝገብ የፌደራል መንግስት እና ክልሎች ከህዝብ ጋር በመምከር አጥፊን እየቀጡ ለለውጥ እየተጉ ነው፡፡ በዚህ ሁሉ አገራዊ የለውጥ ማዕበል ውስጥ ደሴት የሆነ ክልልና ህዝብ ቢኖር ደግሞ ሐረርና ሐረሪ ክልል ነው፡፡ ሃያ አምስት አመት ሙሉ በልማትም በመልካም አስተዳደርም በገዢዎቹ ግፍ እየተፈፀመበት ያለ ህዝብ ቢኖር ሐረር ነው፡፡ ያንን የመሰለ ገናና ስም የነበራት የስልጣኔ አውራ ዛሬ ላለፉት 25 አመታት ባደረገችው የቁልቁለት ጉዞ የሐገር ጭራ ሆና ትገኛለች፡፡ ቀድሞ ሐረር፤ ሐረር ይባል የነበረው አወንታዊ ገፅታዋ ዛሬ በሌሎች የሐገሪቱ ከተሞች ተቀይሯል፡፡ ማንም ስለሐረር መገረምና መደነቅ ካቆመ ከራረመ፡፡ ትውልድና እድገታቸውን በሐረር ያደረጉ በርካታ ወጣቶች ከተማዋን ጥለው መውጣት ብቻ ሳይሆን ላለመመለስ ያላቸው ስሜት ይገርማል፡፡ አንዳንዶቹ የፌደራል ስርዓቱ ያስከተለው ዳፋ እንደሆነ በማሰብ ያማርራሉ፡፡ ባስ ያላቸው ክልሉ በፌደራል አስተዳደር ስር የሚሆንበትን ቀን በተስፋ ይናፍቃሉ፡፡ ራስን በራስ የማስተዳደር መብት ብሎም ዲሞክራሲያዊ አንድነትን የሚያውጀው ህገ-መንግስት የጥቅም እንጂ የጉዳት ምንጭ አልነበረም፡፡ የሐረሪ ህዝብ ብሔራዊ እውቅና አግኝንቶ ራሱን በራሱ ማስተዳደሩም ትክክል ነው፡፡ የነዋሪዎቿ እና ተወላጆቿ ምሬት ግን የልማት እጦት እና የመጥፎ አስተዳደር በደል የፈጠረው ነው፡፡

ከልማት አኳያ ሐረሪ ክልልም ሆነ ሐረር ከተማ ባለፉት 25 አመታት በነበረችበት የቆመች ስለመሆኗ ጥርጥር የለውም፡፡ በነዚህ አመታት ውስጥ በዚህ ክልል የተቀነሰ ካልሆነ የተጨመረ ነገር የለም፡፡ በርግጥ በጥቅም መረብ እና ጠባብ ብሔርተኝነት የታወሩት ገዢዎቿ መስራት ቢያቅታቸው 'ሲጨቁኑን ነበር' ያሏቸው ያለፉት

መንግስታት የሰሯቸውን የልማት ስራዎች ስም ለውጠዋል፡፡ ትምህርት ቤቶችን፤ ስቴዲየሞች፤ ሆስፒታል፤ አዳራሽና ሌላም፡ ሌላም መስራት ቢያቅታቸው ስም መለወጥ ችለዋል፡፡ ለነገሩ በስም እንኳ የሚቀድማቸው ያለ አይመስልም፡፡ የክልሉ ገዢ ቡድን እልም ያሉ ፀረ-ፍትህ ሆነው ሳለ "የሸሪፍ ቡድን" ይላሉ እራሳቸውን፡፡ የነብዩ መሐመድ አስተምህሮ ተከታይ ለማለት ነው፡፡ ባለፉት 25 አመታት በሐረር የተሰራ አንድም ለወሬ የሚበቃ የህዝብ አገልግሎት የሚሰጥ መሰረተ ልማት የለም፡፡ ከአስር አመታት በላይ የውሃ ችግሯን ለመፍታት ተብሎ በስንት ምዝበራ ያለፈው ፕሮጀክት እንኳ ፡ ሊያስታግሳት ካልሆነ የሚፈውሳት እንዳልሆነ በከተማዋ ያለው ሁኔታ ያሳያል፡፡ በ25 አመታት ውስጥ ክልሉን የሚመራው ቡድን ከዚህ የተሻለ ሰራሁት የሚለው አንድም ነገር እንደሌለ በሙሉ ልብ መናገር ይቻላል፡፡ ነዋሪው ግን እያረረም ቢሆን ይቀልዳል፡፡ በ2007 መገባደጃ በመላው አገሪቱ የመጀመሪያው እድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ውጤት የሆኑ ፕሮጀክቶች በአገሪቱ ጠቅላይ ሚ/ር ሲመረቁ በሓረሪ *'ምይንኮን የሚተካ'* ያሉትንና አገልግሎት ከጀመረ አራት አመት ያለፈውን ኩርማን ጋራዥ ሲያስመርቁ ህዝብ እያረረ ይቀልዳል፡፡ ከሌለ ምን ይመረቅልህ? በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች አያሌ ፕሮጀክቶች በክልሎችም በፌደራል መንግስቱም ሲጀመሩና ሲመረቁ፡ ሐረር ምን በወጣት እሄን ታድርግ? እንኳን ለሐገር ፡ለነዋሪዎቿ ማኩረፊያ የሚሆን ቁም ነገር ያለው የልማት ስራ የለም፡፡

ለነገሩ: 25 አመት ሙሉ በፌደራል መንግስት ድጎማ ጭምር በክልሉ ሲመደብ የነበረው የካፒታልና መደበኛ በጀት ምን ያህል እንደሆነ፤ ቢደምሩት ስንት እንደሚሆን ማን ያውቃል? ለምን ተብሎ የተመደበ ነበር? ምንስ ሰሩበት? ማን ያወራርደው?

ባለፉት ስድስት አመታት እየተንከላወሰ እንገነባዋለን ያሉትን የባህል ማዕከል ሐረር ብቅ ላለ ሰው ሁሉ ለጉብኝት የሚጋበዝ የክልሉ "ሜጋ ፕሮጀክት" ብለውታል፡፡ የአንድ ክልል አመራር በልጆች ጨዋታ ዓይነት ሲዳክር እንደማየት አሳፋሪ ነገር የለም፡፡ በእትዕ **1** ምን ሰራችሁ ቢባል የባህል ማዕከል እንደማይሉ እርግጠኛ መሆን አይቻልም፡፡ በዚህ ሁሉ ጊዜ አንድም ፋብሪካ በክልሉ አልተከፈተም፡ አንድም የተጨመረ ት/ቤት፡ ጤና ተቋም በሐረር የለም፡፡ በርግጥ ከሃያ በላይ መስጊዶችን መገንባት የቻለ ክልል ነው፡፡ በተረፈ ሐረር ትናንትም ዛሬም ያው ነች፡፡ በፌደራል የልዩ ድጋፍ ቦርድ ትግል ለመስራት ከተሞከረው የጋራ መኖሪያ ቤት ውጭ በሐረር የሚታይ ምን አለ? ያም ቢሆን በስንት የኪራይ ሰብሳቢዎች ልፊያ ውስጥ ያለ ነው፡፡ በጥቃቅንና አነስተኛ የተደራጁት ድሆች፤ በህብረት ስራ ማህበራት የተደራጁት ወጣቶች የት አካባቢ፤ ምን ያህል ነበሩ? የት ደረሱ? በጥቅም መረብ የተደራጁትን የጀጎል ቤተሰቦቻቸውን ለፌደራል ጎብኚዎች እያሳዩ መሸወድ ቀርቶ፡ ነዋሪው ምን ይላል የሚለውን ማን ጠየቀ? ተፈላጊ ሰዎች በደብዳቤ ተጠርተው ካልሆነ ህዝብ እንደ ህዝብ ምን ይላል የሚል መድረክ መቼ ተደርጎ ያውቃል? አይታሰብም!፡፡ የክልሉ ገዢዎች በሽታ እንደ መንግስት መስራት አለመፍቀዳቸው ብቻ ሳይሆን ሊሰሩ የሚፈልጉትን የሀረሪ ተወላጆችና የከተማዋ ነዋሪዎች የማስተናገድ ቁመና ማጣታቸው ነው፡፡ እንደ እድል

*ሆኖ ሐረሪዎች እጅግ በርካታ የተማሩ የብሄረሰቡ ተወላጆች ቢኖሯትም፣ እስከ ንዑስ ጎሳ በዘለቀው የጥቅም መረብ ግንኙነት ከክልላቸው ጉዳይ እንዲገለሉ ተደርገዋል፡፡ የባሰባቸው በድሬዳዋና አዲስአበባ ኑሯቸውን እየገፉ በክልላቸው ጉዳይ የሩቅ ተመልካች ሆነዋል፡፡ ስለክልሉ ሲነሳባቸውም "መጫወቻ አ'ረጉት! " በማለት ይንገሸገሻሉ፡፡ ኑሯቸውን በሐረር አድርገው አገር ለማልማት ለሚያቀርቡት ጥያቄ የሚሰጠው ምላሽ በህግ ከሚመራ አገር ሳይሆን ከማፍያ ቡድን የማይተናነስ እርምጃ መውሰድ ተለምዷዊ ተግባር ነው፡፡ በእሳት የወደመ የገበያ ማዕከላቸውን ተገቢ ካሳ ማግኘቱ ቢቀር በአክሲዮን ተደራጅተው አቅም አለን እናልማ እያሉ ሲጮሁ የነበሩ በርካቶች፣ የሚዳኛቸው የሊዝም ሆነ የይዞታ ህግ ባለመኖሩ፣ በክልሉ ገዢዎች ምርጫ 'የእኛ ሰው' ላሉት ግለሰብ ተሰጠባቸው፡፡'ገንዘብ ሲናገር ፍትህ ዝም ይላል፡፡'*

*የመጥፎ አስተዳደር ሀገሯ* ወዲህ ነው፡፡ "HOW BAD CAN A GOVERNMENT BE? /*መንግስት ምን ያህል ይከፋል?*" ሲል የጠየቀው ምሁር እንዲህ ዓይነቱን ጉድ አይቶ ይሆናል፡፡ በዚህ ያላበቃው የክልሉ አስተዳደር ከሰባት አመታት በላይ የልማት ጥያቄ ሲያቀርቡ የነበሩ የሸዋበር ነጋዴዎችን፣ በቀዳሚዎቹ ላይ የፈፀመውን ኢፍትሃዊነት ሊደግም ሰሞኑን ተዘጋጅቷል፡፡ በይዞታቸው ላይ ለክልሉ ልማት የሚጠቅም ስራ ለመስራት ለአመታት ሲጠይቁ የነበሩ ባለሃብቶች መብት ተነፍገው፤ የማልማት አቅም እያላቸው፤ የአካባቢው የልማት ፍላጎት(ካለ) ይነገረንና በዚያ መሰረትም የማልማት አቅም አለን እያሉ፣ የክልሉ መሪዎች ግን በተካኑበት የማወሳሰብ ተግባር ሲያደናግሩ ኖረው አሁን *"የእኛ ያሉት"* ፤ *"አልሚ መጥቷልና"* ለቃችሁ ውጡ የሚል ደብዳቤ አድለዋቸዋል፡፡ ምክንያት ሲሉም ከስድስት ወር በኋላ ለሚከበረው *"ለብሄረሰቦች በዓል ሆቴል በፍጥነት እንዲገነባልን ተፈልጓል"* የሚል ነው፡፡ የነ ቶሎ ቶሎ ቤት እንዲህ ያምርበታል፡፡ ህግና ሞራል ሳይሆን ከስዓት በኋላ አብሮ በማሳለፍ ልማድ የህዝብ መስተንግዶ የሚሰጥበት ክልል ነው፡፡ ባለይዞታ ባለሀብቶቹ ግን ሆቴልም ከተፈለገ በቦታው ሆቴል የመገንባት አቅም እንዳላቸው ቢገልፁም ሰሚ የለም፡፡ እስከ አገሪቱ ጠቅላይ ሚኒስትር ይግባኝ ቢሉም፣ ያንን ማድረጋቸው ሌላ መዘዝ አምጥቶባቸዋል፡፡ እንዴት አጋለጣችሁን ይመስላል እንዲያውም በአራት ቀን ውስጥ ካልተነሳችሁ ተብለዋል፡፡ ልዩ ጥቅም እና የግንኙነት መረብ ህዝባዊነትን ደፍጥጣለች፡፡ ለነሱ ልማታዊ ባለሃብት ማለት በመዋቅራቸው ያሉ የመንግስት ደላሎች ናቸው፡፡

በአንድ ወቅት አንዲት የኦሮሞ ብሔር ተወላጅ ቤት የምትገነባበትን ቦታ እንዴት እንዳገኘች ስትናገር *"አፋቸውን ስለምናገር ተወላጅ መስያቸው ሰጡኝ"* ያለችው አይረሳም፡፡ በርግጥ አሁን ቋንቋቸውን ከመናገርም ወርዶ በጎሳና ንዑስ ጎሳ የሚስተዋለው ጠባብነት አስነዋሪ ነው፡፡ በርግጥ መናገሩ ግን በብዙ እጥፍ ቢሮክራሲ ያቀላል፡፡ በነዋሪነት ላልማ ያሉትን እንዲህ ይበድሉ እንጂ በዚህ ክልል ውስጥ የብሔሩ ተወላጅ ወዳጅ ከሆነ በስራ ቦታው ቢገኝም ባይገኝም የደመወዝ ዝርዝር ላይ ግን ስሙ አለ፡፡ ያልሰራን መክፈል "የዜግነት" ይሉታል የሐረሪ አስተዳዳሪዎች፡፡ በሐረር የሚታወቅ እውነት አለ...."*የነሱ ሰው ሶስት መሬት ይወስዳል፤ አንዱን ሸጦ ሁለተኛው*

*ላይ ቤት ይሰራል፤ ሶስተኛው ተሸጦ ንግድ ይጀመራል፡፡"* ተያይዘህ ድህነትን መሰናበት እንዲህ ነው፡፡ እድለኛ ከሆንክ '*የሸሪፍ ቡድን*' ውስጥ ተገኝ፤ ቢያንስ ባጃጅ ይገዛልሃል፡፡ አንድ ባለስልጣን እስከ አምስት መሬት መውሰድ የሚቻለው፤ለወዳጆቹ የቻለውን የሀብት ምንጭ በነፃነት ማስተካከል መቻሉ በርግጥም ልዩ ዜግነት ቢኖር ነው፡፡ *"ስንት ዋጋ ከፍለን ያገኘነውን መብት ብለውም "* ፈገግ ያረጉሃል፡፡ ለዚህ ሁሉ ግን ሐረሪ መሆን ጠቃሚ ቢሆንም ብቻውን ግን አይበቃም፡፡ በወሃቢያ አራማጁ የ'ሸሪፍ ቡድን' ውስጥ መገኘት የግድ ነው፡፡ *"ከሌላው የሐረር ተወላጅ ህዝቡን እየለያያችሁ ነው፤ ተወላጁም ሆነ ዲያስፖራው በክልሉ እንዳያለማ እያደረጋችሁ ነው"* ያሉ የሐረሪ ተወላጆች ሁሉ እጣ ፈንታቸው መገለልና ስደት ሆኗል፡፡ ከሐረር እስከ መርካቶ የእንጀራ ገመድህ ይበጠሳል፡፡ የእነዚህ ወገኖች ጥያቄም *"የሐረሪ ህዝብ በደል አሁን ራሱን በራሱ በሚያስተዳድርበት ወቅት ነው ወይስ ቀድሞ ጨቋኝ ስርዓት በነበረበት?* የሚል ሆኗል፡፡

በርግጥም ያለፈውን የሚያስናፍቅ በደል እና የመልካም አስተዳደር እጦት ሐረሪን እየናጣት ነው፡፡ ከሳሽ ማረሚያ ቤት ተከፍቶለት ተከሳሽን እንዲያበድብ የሚደረገው በዚሁ ክልል በነዚሁ ሰዎች ነው፡፡ ለዚህም ነው ኢትዮጵያንስ ሐረር አያርጋት የምለው፡፡ ሐረርን መሆን በልማት ቆሞ መቅረት ሆኗልና፤ ሐረርን መሆን ጠባብ ብሔርተኝነት የሚጋልበው ኢ-ፍትሐዊነት መገኛ ሆናለችና፡፡ ሐረር *"የዜጋና መጤ"* ማልያ የሚያለብስ አስተዳደር ባለቤት ሆናለችና፡፡ ሐረር የእስላማዊ አክራሪው ወሃቢያ አስተምህሮ መፈልፈያ የምስራቅ አፍሪካ ማዕከል ሆናለችና ኢትዮጵያንስ ሐረር አያርጋት፡፡ በርግጥ የክልሉ መሪዎች በአንድ ነገር ላይ ፍፁም እርግጠኛ ይመስላሉ፡፡ ገንዘብ ለሁሉም መልስ የሚሰጥ አስማተኛ ሆኗል፡፡ እውነታቸውን ነው 25 አመት ሙሉ ስንቱን ጉደኛ ወዳጃቸውን ገንዘብ ታድጎላቸዋል፡፡ ስንቱን ጉልበተኛ ገንዘብ አሸመድምዶታል፡፡ ምንም ቢሰሩ ገንዘብ የሚባል ሁሉን ቻይ ጠበቃ አላቸው፡፡ የዛሬን አያርገውና መቻቻል ይሰበክባት የነበረችው ከተማ፡ በጥቃቅን የት/ቤት እና የመጠጥ ቤት ፀብ እንኳ የክልሉ ገዢ ቡድን ጣልቃ እየገባ የመደብ ፀብ ያደርጉታል፡፡ የክልሉ ደባል ገዢ የሆነው ኦህዴድ የሚያስቀምጣቸው ጥቂት ግለሰቦች በአንድ በኩል አፍ ማስያዣ ሲበጅላቸው በሌላ በኩል የቻሉትን ተመሳሳይ መረብ ለመዘርጋት ይሰራሉ፡፡ ብዙ ሲባልላት የኖረችው ሐረር ዛሬ በሳው'ዲ አረቢያ ጉብኝት እና ልዑካን አቀባበል ስራ የበዛባቸው ባለስልጣናት እጅ ላይ ትገኛለች፡፡ እስከ ባህሬንና ኳታር ለግብዣ የሚጠራ አመራር ሐረሪ ካልሆነ ሌላ ክልል መኖሩን እንጃ፤ የተወላጁን የልማት ጥያቄ ደፍጥጦ ለኳታር ባለሃብት የሚሰግድ አመራር እዚህ እንጂ ሌላ ቦታ አላውቅም፡፡ የቱርኮች እዚያ ሽር ጉድ እስላማዊ ወንድማማችነት መሆኑ ነው፡፡ ቢጤዎቻቸውን ከወራቤ አስመጥተው ዲቤ ላይ ናቸው፡፡ ነገሩ ያልገባው የክልሉ ነዋሪ *"ሐረር እየመጡ ያሉት ሙስሊም ጉራጌዎች (ወራቤዎቹን ማለቱ ነው) ፊት ይሸፋፈናሉ"* ይላል፡፡ *ሐረር-መርካቶ አደሬ ሰፈር- ወራቤ - ሪያድ* ከፍተኛ ትኩረት የሚሻ ዋነኛው የአክራሪው ወሓቢያ/ሰለፊያ መስመር ነው፡፡ በከፍተኛ ገንዘብ የታጀበ ውስብስብ የአክራሪዎች መረብ ነው፡፡ በዚህ ዙሪያ ብዙ ማለት ይቻላል፡፡ በርግጥ በመሬት አስተዳደር፤ በማህበራት አደረጃጀት ፤ በፍትህና ዳኝነት፤ በዘረኛው የክልሉ ገዢ ቡድን እንዲሁም በአክራሪው መረብ ውስጥ በክልሉ ያለውን የመልካም አስተዳደር

ምሬት ፤ የአመራሩን አሻጥርና አስመሳይነት በተከታታይ በዝርዝር ሰነድ አስደግፌ አቀርባለሁ፡፡ መፍትሔ ቢመጣም ባይመጣም እስከመጨረሻው እንጮሃለን፡፡ ትውልድ ይመዘግባል!፡፡ ሐረር የወደቀባትን የልማት በደልና የመልካም አስተዳደር ፈተና እያየ ዝም ያለውን የፌደራል መንግስት የሚታዘቡ ነዋሪዎች፡ 'ትንሽ ናቸው ብሎ ይሆን' በማለት ይሰጋሉ፡፡ "ዝንብ ፡ባይገድል፡ ያስመልሳል " ምክራቸው ነው፡፡